# ቴዲ

ከጌትነት ኖርዌ



የአንድነቱ ዋርድያ
ወረድክ አሉ ዘብ ጥያ
ለጥቅም ባለማደርህ
ለፍቅር በመዘመረህ
ጥላቻን በማውገዝህ
ሃቅን በማስዋጥህ
በባህሉ በሃይማኖቱ
በወግ ልምዱ በእምነቱ
በአንድ እንዲመክር
በአንድ እንዲዘክር
ሳይለያይ በሕብረት
አብሮ እንዲኖር በአንድነት
መዘመርህን የጠሉት
በጠባቡ ቦይ የፈሰሱት
አመካኝተው ሊበሉህ
ቂማቸውን ተወጡብህ
ፍትህ ርትዕ በሌለበት
ምን ይባላል እንዲህ መብከት
ጊዜ የሰጠው ቅል እንዲሉ
የተናቀ .... ቢሉ
ቲፒም ገዛች

በሕዝብ እናት ላይ ደነሰች
ታጋይ አንበሶቹን አጋዘች
በጉድጓድ እሥርቤት አጎረች
እናም ቴዲ አይዞህ በርታ
ያንተ ነንና አታመንታ